የሰበር መ/ቁ. 19958

ግንቦት 4/1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. " ጌታቸው ምህረቱ

4. " መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ አስፋው ማናዬ

ተጠሪ፡- የኢት/ንግድ ባንክ ጊምቢ ቅርንጫፍ

## ፍ ር ድ

ለሠበር መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በም/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከተጠሪ ባንክ ለተበደሩት ብድር ያስያዙት ቤት ከግምቱ በታች ለመሸጥ ጨረታ በመውጣቱና በዋስትና ያልተያዙ ቤቶች ጭምር በጨረታ እንዲሸጡ ማስታወቂያ በመውጣቱ ጨረታው እንዲቆም ክስ አቅርበዋል:: ጉዳዩን ያየው ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ክስ ባለመቀበል ጨረታው እንዲቀጥል ወስኗል:: የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል::

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ተጠሪ በዋስትና ከያዘው ቤት ውጪ አመልካች ለተበደሩት ብድር መክፈያ ሌሎች ቤቶችን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በጨረታ እንዲሸጡ ማስታወቂያ መውጣቱ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሠምቷል::

በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የሚንቀሣቀስ ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት በዋሰትና የያዘ ባለገንዘብ ባንክ የሚፈልገው እዳ በተወሰነው ጊዜ ካልተከፈለው ማስጠንቀቂያ ለባለዕዳው በመስጠት በመያዣ የያዘውን ንብረት በሀራጅ ለመሸጥ ይችላል :: /አንቀጽ 3 ይመለከታል/ በመሆኑም በዚህ አዋጅ መሠረት ባንክ ላልተከፈለው እዳ ንብረት ሊሸጥ የሚችለው ቀድሞውኑ ንብረቱን ለብድሩ በዋሰትና ወይም በመያዣ የያዘው ከሆነ ነው::

13-10-98

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለአመልካች ላበደረው ብድር በአዋጁ መሠረት ጨረታ ያወጣው በአራት ቤቶች ላይ ማለትም በቤ/ቁ/418፣ 468፣ 465፣ እና 480 ላይ ነው ፡ የአመልካች ዋነኛ ክርክር የቤ/ቁ/465 እና 480 ለበድሩ በዋስትና የተሰጡ አይደሉም የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህ ችሎት ባንኩ እነዚህን ክርክር የተነሣባቸውን ቤቶች በመያዣ የያዘው መሆኑን ለማረገገጥ የማያዣ ውሉን ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ባንኩ ለአመልካች ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘው ባባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር 02/86 የተመዘገቡትን የቤት ቁጥር 418፣ እና 468 ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የቤት ቁጥር 465 እና 480 በመያዣ የተያዙ ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆን የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ባንኩ በአ/ቁ/97/90 መሠረት ራሱ ጨረታ በማውጣት ንብረት ሊሰጥ የሚችለው፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ ንብረቱን ለሰጠው ብድር በመያዣ ይዞታ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውል ደግሞ በጽሁፍ መሆንና መመዝገብ ያለበት በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ/1723 እና 3045 ይመለከታል) ተጠሪ ቤቶቹን በመያዣ የያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ በጽሁፍ የተደረገና የተመዘገበ የመያዣ ውል ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን በሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪው የቤ/ቁ/465 እና 480 በመያዣ የያዘው መሆኑን ሳያረጋግጡ ቤቶቹ ላይ የወጣው ጨረታ እንዲቀጥል መወሰናቸው ህጉን ያልተከተለ መሆኑን ተረድተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የም/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 184/94 በ24/2/96 እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/02605 በ20/7/97 የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2/ ተጠሪ ጨረታውን ለቤ/ቁ/418 እና 468 ላይ ብቻ እንዲቀጥል፡፡ በመያዣ ያልተያዙት ቤቶች ላይ ማለትም ከቤ/ቁ/465 እና 480 በጨረታ ሊሸጡ አይገባም ፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

ተ.ወ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ________ ቀን 13-10-98

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት